Arlington Public Schools

STAFF CENTRAL



# የAPS የኃላፊ የውሳኔ ሃሳብ የረጅም ጊዜ ዕቅድ እና የውሳኔ ሃሳብ

#APSPLANS2021

# ትምህርት ቤት ሲቀየር የሚነሱ የተለመዱ ጥያቄዎች

**ጥያቄ፡-** አማራጭ ትምህርት ለሚከታተሉ ተማሪዎች መላ አገሪቱን የሚሸፍን ትራንስፖርት መስጠቱ ይቀጥላልን?

**መልስ፡-** አዎ፡፡

**ጥያቄ፡-** ከ ATS ወደ ማክኬንሊ ልጁ መዘዋወሩ የአውቶቢስ ጉዞዉን ከ 15 እስከ 20 ደቂቃዎች ከፍ ያደርገዋልን?

**መልስ፡-** የሁለቱን ትምህርት ቤቶች አድራሻ የሚያሳየው በሁለቱ መካከል የ 5 ደቂቃዎች ልዩነት እንዳለ ነው ርቀታቸው 2 ማይል ያክል ስለሆነ፤ ይህ የጊዜ ልዩነት ልጆቻቸውን ነድተው ወደትምህርት ቤት ለሚወስዱም ወላጆችም ጭምር ነው፤ ከሁሉም ቦታ ተነስተው ወደ ትምህርት ቤቱ ለሚመጡት ጊዜ ለመቀነስ ለተወሰኑ ፕሮግራሞች APS ተጨማሪ መገናኛ ማቆሚያዎችን መጠቀም ይጀምራል፤ መገናኛ ማቆሚያዎችም አውቶቢሶች የሚቆሙበትን ቦታ ያጠቃልላሉ እና ማዕከላዊ እንዲሆኑ ያደርጋሉ በዛ ያሉ ተማሪዎችን በአንድ ጊዜ ለማሳፈር ሲባል፤ አውቶቢሶቹን ለሞምላት የተሻለ ሁኔታም ይፈጥራል እናም የጉዞ ጊዜንም ይቀንሳል፡፡

**ጥያቄ፡-** የትምህርት ቤት ቦርድ ይህንን ሃሳብ ካጸደቀው፣ መቼ ነው ተፈጻሚ የሚሆነው?

**መልስ፡-** ከበልግ 2020 የማኅበረሰብ ሂደት ጋር በተያያዘ ትምህርት ቤቶች የቦታ ቅያሪ ወይም ዝውውር የሚያደርጉት በሴፕቴምበር 2021 ይሆናል፡፡ APS ማናቸውንም ልውውጦች ከሚያደርጉ ማኅበረሰቦች ጋር አብሮ ይሰራል፡፡

**ጥያቄ፡-** ቀጣይ የተሳትፎ ዕድሎች ምንድን ናቸው?

**መልስ፡-**

- ጃንዋሪ 30 ቀን 2020፡- የትምህርት ቤት ቦርድ ሕዝባዊ ስብሰባ በታላፊው የውሳኔ ሃሳብ ላይ
- ፌብርዋሪ 6 ቀን 2020፡- የትምህርት ቤት ቦርድ በታላፊው የውሳኔ ሃሳብ ላይ እርምጃ ለመውሰድ ቀጠሮ ይዟል እንዲሁም ቤተሰቦች አስተያየቶቻቸውን እና ጥያቄዎቻቸውን በ engage@apsva.us ሊልኩልን ይችላሉ፡፡

Arlington Public Schools

# ምልከታ፡- የረጅም ጊዜ ዕቅድ

- ሠራተኞች በጠቅላላው ለማሕበረሰቡ ጠቃሚ የሆኑ የረጅም ጊዜ መላ አገሪቱን የሚሸፍን ዕቅድ የማውጣት ኃላፊነት አለባቸው፡፡
- ከጸደይ ወቅት 2018 ጀምሮ፣ APS ፕላኒንግ እነዚህን የረጅም ጊዜ ተግዳሮቶች እንዴት መፍታት እንደሚችል ከግምት አስገብቷል፡-
  - በመላ አገሪቱ ተማሪዎች በሚኖሩበት ስፍራ እና በአካባቢው ያሉ ቦታዎችመካከል ልዩነት ያለ በመሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ  ትምህርት ቤት ሕንጻዎችን በውጤታማነት መጠቀም
  - በ Rosslyn-Courthouse፣  በ Columbia Pike እና በ Route 1 መተላለፊያዎች ይኖራል ተብሎ ከሚጠበቀው ፈጣን ዕድገት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አቅም መፍጠር
  - እያደገ የመጣው የAPS የአውቶብስ አገልግሎት እና ግብዓቶች ፍላጎት ለማስተናገድ አንዲያግዝ የትምህርት ቤቶች መከታተያ ዞኖች ማቋቋም፡፡
- APS እነዚህን ተግዳሮቶች ለመፍታት፣ አራት ደረጃዎች ያሉት ሂደት በመጠቀም ላይ ነው

#APSPLANS2021

# ምልከታ፡- የረጅም ጊዜ ዕቅድ ደረጃ 1፡፡

- ይህ የወቅቱ ሂደት የባውንደሪ ሂደት አይደለም
- በዚህ ደረጃ 1 ትምህርት ቤቱ ለረጅም ጊዜ ተግዳሮቶች ምላሽ ለመስጠት እና በልግ 2020 የባውንደሪ ሂደት መሠረት መጣል
- ከሕንጻዎቻችን መካከል የአንዳንዶቹን አገልግሎት በመቀየር APS ከዚህ ለሚከተሉት ዓላማዎች ድንበሮችን እንዲያስቀምጥ ይረዳዋል፡-
  - በመላ አገሪቱ በተቻለ መጠን ለበርካታ ተማሪዎች በቅርብ የሚገኘው አካባቢ ትምህርት ቤት ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ
  - ለእግር ጉዞ ያለን ምቹነት ከፍ ማድረግ
  - እየጨመረ ያለውን የትራንስፖርት ወጪ ማስተናገድ
  - የተማሪዎችን የአውቶብስ ረጅም ጉዞ መቀነስ
- በመላ አገሪቱ በበልግ 2020 ሂደት የተዘጋጁ ድንበሮች ስድስት አባላት ባሉት የትምህርት ቤት ቦርድ በተቀመጠው የፖሊሲ ግብዓት መሠረት ነው፡፡

#APSPLANS2021

# ደረጃ 1 - የትምህርት ቤት ዝውውር
## ከኖቬምበር 2019 እስከ ፌብርዋሪ 2020

| መፈታት ያለባቸው ተግዳሮቶች | የAPS ዓላማዎች | የማኅበረሰብ ተሳትፎ | የመጨረሻ እርምጃ |
|---|---|---|---|
| በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የአካባቢ እና በመላ አገሪቱ ተማሪዎች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ያለ የተማሪ ቦታዎች ልዩነት | • ለትምህርት ቤት ዲቪዚዮን በጠቅላላ የረጅም ጊዜ ዕቅድ<br>• APS ስድስቱን የSB ፖሊሲ ከግምት ውስጥ በማስገባት ድንበሮችን ለማስቀመጥ እንዲችል የበልግ ባውንደሪ ሂደት መሠረት መግንባት<br>• በBallston መተላለፊያ የአካባቢ ትምህርት ቤት አቅም መፍጠር | • ስለተግዳሮቶች እና ዓላማዎች ማኅበረሰቡን ማሳወቅ<br>• ሃሳቦችን መጋራት እና የሚገኘውን ግብዓት የመጨረሻ የውሳኔ ሃሳብ ለማቅብ መጠቀም እንዲሁም በቀጣይ ደረጃዎች ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ጉዳዮችን መፈተሽ፡፡ | ፌብርዋሪ 6፡- በ2021-22 ማክኬንሌይን፣ ATS እና ኪን ወደ አዲስ ስፍራዎች ለማዘዋወር በኃላፊው በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ላይ በቦርዱ ድምጽ ጸሰጣል |

#APSPLANS2021

# ደረጃ 2 – የዕቅድ ክፍል (PU) የመረጃ ክለሳ

*ከማርች እስከ ጁን 2020*

| መፍትሔ የሚያሻቸው ተግዳሮቶች | የAPS ዓላማዎች | የማኅበረሰብ ተሳትፎ | የመጨረሻ እርምጃ |
|---|---|---|---|
| በበልግ ወቅት ከሚካሄደው የባውንደሪ ሂደት በፊት በፕሮግራም ክፍል ደረጃ የመረጃዎችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ | • የዕቅድ ክፍል መረጃዎችን ለመከለስ ወይም ለመመልከት ከማኅበረሰቡ ጋር መሥራት<br>• ከሁሉም የባውንደሪ ሂደቶች በፊት ማናቸውንም የሚፈለጉ ማስተካከያዎች ማድረግ | የአካባቢ የዕቅድ ክፍልን መረጃዎች በመከለስ ረገድ PTA፣ ሲቪክ ማኅበራት እና ሌሎች ከ APS ጋር አብረው እንዲሰሩ እና ክለሳ በሚያሻቸው ጉዳዮች ላይ ግብዓት ያቀርባል | በበልግ የባውንድሪ ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ መረጃዎች በኦገስት 2020 ይጠናቀቃሉ፡፡ |

#APSPLANS2021

# ደረጃ 3 - የባውንደሪ ሂደት

## ከሴምፕቴምበር እስከ ዲሴምበር 2020

| መፍትሄ የሚያሻቸው ተግዳሮቶች | የAPS ዓላማዎች | የማኅበረሰብ ተሳትፎ | የመጨረሻ እርምጃ |
|---|---|---|---|
| • በመላ ትምህርት ቤቶች የአቅም አጠቃቀም ሚዛናዊ አለመሆን<br>• የአዲስ ትምህርት ቤት መከፈት<br>• ከክትትል ዞኑ ውጪ ጨሆኑ<br>• ብቁነት ላላቸው ተማሪዎች እና በመላው ትምህርት ቤቶች የመዋዕለ ሕጻናት ትምህርት ቤት ማቀድ | • ለ2021-22 ባውንደሪዎች ለማጎልበት በAPS ባውንደሪዎች ፖሊሲ B-2.1 ግብዓቶችን መጠቀም፡፡<br>• ከዚህ ለሚከተሉት የክትትል ዞን መፍጠር ወይም ለመመስረት<br>o በሪድ ሳይት አዲስ ትምህርት ቤት<br>o አካባቢውን የሚያካትቱ ASFS<br>• በሁሉም ትምህርት ቤቶች አቅምን ለማስተዳደር ወደሚቻልበት ደረጃ ማምጣት<br>• ብቁ ከሆኑ ተማሪዎች አቅራቢያ ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች ለቅድመ መዋዕለ ሕጻናት ትምህርት ቤት የመማሪያ ክፍል ቦታ መኖሩን ማረጋገጥ | ሃሳብን ማጋራት እና የመጨረሻ የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ እና በቀጣይ ደረጃዎች ምላሽ የሚያሻቸውን ችግሮች ለመለየትግብዓት የሚሆኑ ሀሳቦች መቀበል፡፡ | ዲሴምበር (TBD)፡- ኃላፊው በ2021-22 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ባውንደሪዎች ላይ የትምህርት ቤቱ ቦርድ ድምጽ ይሰጣል፡፡ |

#APSPLANS2021

# ደረጃ 4 - ዝውውርን በተመለከተ ከትምህርት ቤት ማኅበረሰቦች ጋር አብሮ መስራት

## *ከማርች 2020 እስከ ሴፕቴምበር 2021* **2021**

| መፍትሄ የሚያሻቸው ተግዳሮቶች | የAPS ዓላማዎች | የማኅበረሰብ ተሳትፎ | የመጨረሻ እርምጃ |
|---|---|---|---|
| የዝውውር ሎጂስቲክስ፣ ለምሳሌ ትራንስፖርት፣ ሬፍሬሾች መገንባት እና የፕሮግራም ጉዳዮች | • በቀጣይ የሚደረጉ ለውጦችን፣ የጊዜ ሰሌዳን እና የተሳትፎ ዕድሎችን በተመለከተ ለቤተሰቦች እና ሠራተኞች ማሳወቅ<br>• በትምህርት ቤት ዝውውር ፍላጎቶችን እና ግብዓቶችን መወሰን<br>• በሚያስፈልግ ማናቸውም የስም ለውጦች ላይ ከትምህርት ቤት ማኅበረሰቦች ጋር አብሮ መስራት | TBD - ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር እና PTA ጋር በጋራ ይወሰናል፣ ማዕከላዊ መሥሪያ ቤቶች ድጋፍ ያደርጋሉ | በሴፕቴምበር 2021 ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ዝግጁ ሆነው ክፍት ይሆናሉ |

#APSPLANS2021

Arlington Public Schools

# የረጅም ጊዜ ዕቅድ፡- ዕድገት በመላ አገሪቱ




- APS የመኖሪያ ቤቶች ልማት እና የልደት ምጣኔን በተመለከተ የአርሊንግተን ካውንቲን መረጃ ይጠቀማል
- ለ APS የጅም ጊዜ ዕቅድ የመኖሪያ ቤቶች ልማት ወሳኝ ነው
- ዕድገት በሜትሮ መተላለፊያዎች አካባቢ የተከማቸ ነው፡-
  - Rosslyn/Ballston
  - በColumbia Pike አቅጣጫ
  - Route 1
- ለ2019 እስከ 2019  አዳዲስ አሃዶች ይጠበቃሉ

Arlington Public Schools

# የኃላፊው የውሳኔ ሃሳብ - የትምህርት ቤት ዝውውር




- ይህ የውሳኔ ሃሳብ ምንም ዓይነት የባውንደሪ ማሻሻያዎች አያካትትም፡፡ ፕሮግራም እና አዲሶቹን የትምህርት ቤት ቦታዎች ያካተተ ነው፤ ይህም የሚያገለግለው በበልግ ወቅት የትምህርት ቤት ቦታ ለባውንደሪ ሂደት በተሻለ ለመዘጋጀት ያስችላል፡፡

- የትምህርት ቦት መገኛ ለውጥ የውሳኔ ሃሳብ (ከአዲሱ የትምህርት ቤቶች ባውንደሪዎች እና 725 አዳዲስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መቀመጫ ሪድ መገኛ ጋር አብሮ በሚሄድ መልኩ ከ2021-22 ተፈጻሚ የሚሆን)፡-
  - ብዙዎቹ የማክኪንሌ ተማሪዎች ከርዕሰ መምህር እና ሠራተኞች ጋር ወደ ሪድ ሳይት ይዘዋወራሉ
  - ሁሉም የኢምርሽን ማኅበረሰብ ከ ATS ሳይት ሊዘዋወሩ ይችላሉ
  - ኪ ሳይት አዲስ የአካባቢ ትምህርት ቤት ይሆናል

# የኃላፊው የውሳኔ ሃሳብ – የትምህርት ቤት ዝውውር

**ኃላፊው የትምህርት ቤቶችን ዝውውር አስመልክቶ የሰጡት የውሳኔ ሃሳብ ከዚህ የሚከተሉትን ያደርጋል፡-**

- መሠረት መጣል እና የበልግ 2020 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የባውንደሪ ሂደት በተማሪዎች ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ መቀነስ
- በመላ አገሪቱ በመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች መቀመጫ ወይም ቦታ እና በተማሪዎች መካከል ያለውን አለመመጣጠን ለመፍታት የረጅም ጊዜ ዕቅድ ማስቀመጥ
- አዲስ ትምህርት ቤት ለመገንባት ወይም ለመጨመር የካፒታል ግብዓቶች ወይም ኃብቶች መጠቀም ሳያስፈልግ በሴፕቴምበር 2021 በ Rosslyn-Courthouse አካባቢ የአካባቢ መቀመጫዎች ወይም ቦታዎች ማዘጋጀት
- ተማሪዎች በአውቶብስ መሳፈር ሳያስፈልጋቸው በአካባቢው ወደሚገኙ ትምህርት ቤቶች በእግር መሄድ እንዲችሉ ለ APS አውቶብስ አገልግሎት እና ግብዓቶች ወይም ኃብቶች ያለውን ፍላጎት ማስተናገድ፡፡
- በመላው አገሪቱ ያለውን ኢመርሽን ወደ ማዕከላዊ ቦታ፣ በተለይም የስፔን ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች ወደሚማሩበት አቅራቢያ እንዲመጡ ማድረግ እንዲሁም ፕሮግራሞችን በ50-50 ድርብ ቋንቋ ሞዴል መደገፍ፡፡
- ተጨማሪ ተማሪዎች ሰፋ ባለ ሳይት እንዲገቡ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት በመላው አገሪቱ ያለውን የATS ተደራሽነት ማስፋት፤ ይህም ፕሮግራሙ ብዝሃነት እንዲኖረው ለማድረግ ያስችላል፡፡